የሰ/መ/ቁ 43069

ሚያዝያ 6 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** አቶ አማረ ረታ - ወ/መላኩ ረታ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ ሰለሞን ካሣዬ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ የቀረበው ክርክር የኑዛዜ ወራሽ እና ያለኑዛዜ ወራሽ የሟች ንብረት ይካፈሉ ሲል የሥር ፍ/ቤት የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የህግ ትርጉም ስሕተት የተፈፀመበት ነው ሲል አመልካች አቤቱታ በማቅረቡ ነው፡፡

የአሁን አመልካች ሟች አቶ ካሣዬ ክፈተው ግንቦት 23 ቀን 1992 ዓ.ም ያደረጉትን የኑዛዜ ስጦታ መሠረት በማድረግ በአቃቂ ክ/ከተማ ቀበሌ 01 የሚገኝ መኖሪያ ቤት ይዞ ያለ ሲሆን ተጠሪ በሥር ፍ/ቤት የሟች ወራሽ መሆናቸውን ጠቅሰው አመልካች ቤቱን እንዲለቅላቸው ዳኝነት ጠይቀው ነበር፡፡ የሥር ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ሟች ተወላጅ እያላቸው ከውርስ የነቀሉ ስለመሆኑም በቂ ምክንያት ሳይሰጡ ያላቸውን ንብረት ለአመልካች በኑዛዜ ማስተላለፋቸውን ጠቅሶ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 939/3/ መሠረት በኑዛዜ ወራሽ እና ያለኑዛዜ ወራሾች ንብረቱን እኩል ይካፈሉ ሲል ወስኗል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ቀርቦለት የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ አፅንቷል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት ተፈጽሟል በማለት ታህሳስ 9/2001 ዓ.ም የተፃፈ አቤቱታ አቅርቧል፡፡ የሰበር አቤቱታው ይዘት ባጭሩ ለአመልካች በኑዛዜ የተሰጠው የሟች ጠቅላላ ንብረት ሳይሆን አንድ መኖሪያ ቤት ብቻ ነው በሚል የሥር ፍ/ቤት የጠቅላላ የውርስ ስጦታ ነው በሚል የፍ/ብ/ህግ ቁ 939/3/ ያለአግባብ ትርጉም ሰጥቷል በማለት እንዲታረም ጠይቋል፡፡

ይህ ሰበር ችሎትም አቤቱታውን ከመረመረ በኋላ በሟች የተሰጠውን ኑዛዜ የሥር ፍ/ቤቶች በማለፍ ጉዳዩን በፍ/ብ/ሕግ ድንጋጌ ቁ. 939 እና 852 መሠረት መወሰናቸው በአግባቡ ስለመሆኑ ለመመርመር ተጠሪን አስቀርቧል፡፡ ተጠሪም ነሐሴ 15 ቀን 2001 ዓ.ም ጽፎ ባቀረቡት መልስ ያለኑዛዜ ወራሾች በሕጉ አግባብ ከውርስ ያልተነቀሉ ስለመሆኑና ሟችም ከተጠቀሰው ቤት ሌላ ንብረት የሌላቸው መሆኑን ጠቅሶ የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ እንዲፀና ጠይቋል፡፡

እኛም ይህንኑ የግራ ቀኙን ክርክር መሠረት አድርገን ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ከሕጉ አገናዝበን መርምረናል፡፡ ከፍ ሲል እንደተመለከተው አመልካች በኑዛዜ የተሰጠውን ቤት ለብቻው ለመውሰድ የሚከራከር ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ የሟች ያለኑዛዜ ወራሽ መሆኑን ጠቅሶ ከኑዛዜው ተጠቃሚ ጋር በሥር ፍ/ቤት በተወሰነው አግባብ ለመካፈል እንዲወሰን ጠይቋል፡፡

በዚህ ፍ/ቤት ውሳኔ የሚያሻው ጉዳይ ሟች ለአመልካች ያደረጉት የኑዛዜ ስጦታ የጠቅላላ ውርስ(ስጦታ) ወይንስ ተለይቶ የታወቀ ንብረት ስጦታ ተብሎ ሊወሰድ ይገባል የሚለው መሠረታዊ ጉዳይ ነው፡፡ በዚህ ረገድ አመልካች አንድ መኖሪያ ቤት ብቻ ነው በኑዛዜ የተሰጠኝ ሲል ተጠሪ ደግሞ ሟች ከዚህ ቤት ሌላ ንብረትም የላቸውም በማለት ተከራክሯል፡፡

ይህንን መሠረታዊ ጉዳይ ለመፍታት የኑዛዜ ሰነዱን አጠቃላይ ይዘት ማየት ተገቢ ሆኖ አግኝተናል፡፡ ሟች ካሣዬ ክፈተው ግንቦት 23 ቀን 1992 ዓ.ም ያደረጉት ኑዛዜ እንደሚያመለክተው የወለዷቸው ልጆች እንዳልጠየቋቸው ጠቅሰው ያላቸውን ቤት ከነጣሪያው ከነግድግዳው ከነአፈሩ ለክርስትና ልጃቸው ለአማረ ረታ የተናዘዙ መሆኑን ነው፡፡ ከዚህም ሌላ ቤት ውስጥ ያለ እቃ የኔነው ያለችውን ሚስት እንድትወስድ እንዲሁም በመንግሥት ተወርሷል የተባለ አንድ ክፍል ቤት ለሚስት ወ/ሮ እናት መንግሥቱ መስጠታቸውን ነው፡፡ ሚስት በሕይወት እስካለች ተጠቅማ በኋላ ለአቶ አማረ ረታ እንድታስረክብ የሚል ሀሳብ ተጨምሮ ይገኛል፡፡

እንግዲህ ከዚህ የኑዛዜ ሰነድ ይዘት መረዳት የሚቻለው ሟች አለኝ ያሉትን ንብረት ጠቅሰው የተናዘዙ ስለመሆኑ ነው፡፡ በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 911(1) እንደተደነገገው የሟች ተወላጆች እንዳያገኙ በማሰብ ያለውን ንብረት አጠቃሎ ለኑዛዜ ተጠቃሚ ስጦታ ያደረገ መሆኑ ሲታይ ሟች ያለውን ንብረት አጠቃላይ ያስተላለፈ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ በዚህ መልክ ያለውን ንብረት ዘርዝሮ ጠቅላላ በኑዛዜ ስጦታ ያስተላለፈ እንደሆነ ደግሞ ኑዛዜው ጠቅላላ ኑዛዜ ሊባል እንደሚችል ከፍ/ብ/ሕግ ድንጋጌ ቁጥር 912(1) መረዳት ይቻላል፡፡

ስለሆነም አመልካች የጠቅላላ ኑዛዜ ተጠቃሚ ነው በሚል በሥር ፍ/ቤት የተደረሰው ድምዳሜ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት አለው ሊባል የሚችልበት ምክንያት አላገኘንም፡፡

አመልካች የሟች ተወላጅ (ያለኑዛዜ ወራሽ) አለመሆኑ አላከራከረም፡፡ አመልካች በጠቅላላ ኑዛዜ የሟች ሀብት በስጦታ የተላለፈለት መሆኑ ከተረጋገጠ በሌላ በኩል ሟች ተወላጆቹን (ያለኑዛዜ) ወራሾችን ከውርስ የነቀለበት ሕጋዊ ምክንያት የሌለ ስለመሆኑ በሥር ፍ/ቤት የተረጋገጠ መሆኑ ሲገናዘብ በዚህ ንብረት ላይ በኑዛዜ ወራሽ እና ያለ ኑዛዜ ወራሾች መካከል የሚኖረው መብት ምን ሊሆን ይገባል የሚለው ጥያቄ አስመልክቶ የሥር ፍ/ቤቶች በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 939/3/ መሠረት መወሰናቸው ከመዝገቡ ተመልክተናል፡፡ ወደዚህ ድምዳሜ ለመድረስ የሚቻለው በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 915/1/ የተመለከተው ሁኔታ ተሟልቶ ሲገኝ እንደሆነ ነው፡፡ ከፍ ሲል እንደተመለከትነው አመልካች በኑዛዜ ጠቅላላ ስጦታ የተሰጠው ሲሆን ተጠሪ ደግሞ ያለኑዛዜ የመጀመሪያ ደረጃ የሟች ወራሽ ነው፡፡ ይህ ከተሟላ ስለክፍፍሉ ሥርዓት የሚወሰነው ደግሞ መርሁ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 939/3/ ይሆናል፡፡

ስለሆነም የሥር ፍ/ቤቶች ይህንኑ የህጉን ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ ተከትሎ የሰጡት ፍርድ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ሊያሰኝ የሚያስችል ምክንያት የለውም፡፡

ስለሆነም የሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ባለበት ሊፀና ይገባል ብለናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

የፌዴራል የመ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 09965 ሚያዝያ 10 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 68488 የሰጠው ፍርድ ፀንቷል፡፡

ግራቀኙ በዚህ ፍ/ቤት ለተደረገው ክርክር የየራሳቸውን ወጪና ኪሣራ ይቻሉ ብለናል፡፡